# የኢትዮጵያ የምግብ እና የመድኃኒት ባለሥልጣን

## የምግብ ጨው ቁጥጥር

## መመሪያ

## 361/2013

የካቲት 2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ


ማውጫ ........ ii
መግቢያ ........ 1
ክፍል አንድ ........ 2
ጠቅላላ ........ 2
1. አጭር ርእስ ........ 2
2. ትርጓሜ ........ 2
4. የተፈፃሚነት ወሰን ........ 3
ክፍል ሁለት ........ 4
ስለ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እና የገበያ ፈቃድ ........ 4
5. ስለ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አስፈላጊነት ........ 4
6. ስለ ነጥብ አሰጣጥ ሂደት ........ 4
7. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች ........ 5
8. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለ ማይጠየቅባቸው ሁኔታዎች ........ 6
9. የአድራሻና የባለቤትነት ለውጥ ስለማድረግ ........ 6
10. ምትክ ስለ ማግኘት ........ 6
11. ስለ እድሳት ........ 6
12. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አቀማመጥ ........ 7
ክፍል ሦስት ........ 7
ስለ ማምረቻና ማከማቻ ህንፃ አሰራርና አስፈላጊ መሳሪያዎች ........ 7
13. ስለ ህንፃ አሰራር ሁኔታ ........ 7
14. ስለ አስፈላጊ መሳሪያዎችና ግብአቶች ........ 9
ክፍል አራት ........ 11
ስለ ቴክኒካል ባለሞያዎች፣ የሞያ ክህሎት እና ጤንነት ........ 11
15. ስለ ቴክኒካል ባለሞያ ........ 11
16. ስለ ሰራተኞች ጤናና ንፅህና አጠባበቅ ሁኔታ ........ 12
ክፍል አምስት ........ 13
የምግብ ጨው ስለ ማምረት፣ በድጋሜ ማሸግ፤ ማስመጣት፣ መላክና ጅምላ ማከፋፈል ........ 13
17. የምግብ ጨው ስለማምረት ........ 13

18. ስለ ጨው ማበልፀጊያ ውህዶች ...... 14
19. ስለ የአዮዲን መጠንና በካይ ነገሮች ...... 14
20. የምግብ ጨው ስለ ማሸግ ...... 15
21. ስለ ገላጭ ፅሁፍ ...... 15
22. የምግብ ጨው ወደ ሀገር ውስጥ ስለማስገባት ...... 17
23. የምግብ ጨው ወደ ውጭ ሀገር ስለ መላክ ...... 17
24. የምግብ ጨው ስለ ማከፋፈል ...... 18
25. የምግብ ጨው ስለ ማከማቸት ...... 18
26. የምግብ ጨው ስለ ማጓጓዝ ...... 19
27. አዮዲን የሌለው ጨው በጥቅም ላይ ስለማዋል ...... 19
ክፍል ስድስት ...... Error! Bookmark not defined.
ድጋሜ ማሸግ ላይ የተሰማሩ ተቋማት ማምረቻ ህንፃ፤ ማከማቻ ቦታና አስፈላጊ መሳሪያዎች ...... Error! Bookmark not defined.
28. ስለ ህንፃ አሰራር ሁኔታ ...... Error! Bookmark not defined.
29. ስለ አስፈላጊ መሳሪያዎችና ግብአቶች ...... Error! Bookmark not defined.
30. ስለ ቴክኒካል ባለሞያ ...... Error! Bookmark not defined.
ክፍል ሰባት ...... 20
አስተዳዳራዊ እርምጃዎች ...... 20
31. ማስጠንቀቂያ ስለ መስጠት ...... 20
32. ስለ እገዳ ...... 20
33. ስለ ስረዛ ...... 21
34. የምግብ ጨውን ሰለ መያዝ ...... 22
35. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለ መመለስ ...... 22
36. እገዳና ስረዛ ስለማንሳት ...... 23
37. የምግብ ጨው ለሌላ አካል ስለማስተላለፍ ...... 23
38. የምግብ ጨው ከገበያ ላይ ስለ መሰብሰብ /Product recall/ ...... 23
39. የተበላሸ ወይም ተፈላጊውን ደረጃ ስለ ማያሟላ የምግብ ጨው ...... 24
40. አስተዳዳራዊ እርምጃዎች አወሳሰድና ቅሬታ አቀራረብ ...... 24
ክፍል ስምንት ...... 25
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ...... 25
41. መረጃ ስለ መያዝ ...... 25

43. የምግብ ጨው ስለ ማስተወወቅ ..... 25
44. መረጃ ለሕዝብ ይፋ ስለ ማድረግ ..... 25
45. ስለ አግልግሎት ክፍያ ..... 26
46. የመተባበር ግዴታ ..... 26
47. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎች ..... 26
48. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ ..... 26
እዝል ..... 27
የኢትዮጵያ የምግብና የመድኃኒት ባለስልጣን በአዮዲን የበለጸገ ጨውን በድጋሜ ማሸግ (ማምረት) ስራ ላይ የተሰማራ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት መጠየቂያ ቅፅ .... Error! Bookmark not defined.
በአዮዲን የበለጸገ የምግብ ጨውን በድጋሚ ማሸግ (ማምረት) ስራ ላይ የተሰማሩ መለስተኛ ድርጅቶች ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች የኢንስፔክሽን ቼክ ሊስት ..... 32

## መግቢያ

ለምግብነት እንዲሁም ለምግብ ማምረቻ ፋብሪካዎች የሚቀርብ ጨው በሀገራዊ ደረጃው ላይ የተቀመጠውን የጥራት ደረጃ እና የአዮዲን ይዘት ጠብቆ መድረሱን ለማረጋገጥ፤

ከአዮዲን ንጥረ ነገር እጥረት ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ የጤና እክሎችን ለመከላከል፣ በምግብ ጨው ማምረት፣ ማሸግ፣ መላክ፣ ማስመጣት እና ጅምላ ማከፋፈል ንግድ ሥራ ላይ የሚሰማራ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በምግብና መድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011 አንቀፅ 71 (2) መሰረት ይህ በአዮዲን የበለጸገ የምግብ ጨው ቁጥጥር መመሪያ ወጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ

## 1. አጭር ርእስ

ይህ መመሪያ “የምግብ ጨው ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 361/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

በአዋጁና ደንቡ ላይ የተቀመጡት ትርጉሞች እንደተጠበቁ ሆነው የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ

1) “አዮዲን ያለው የምግብ ጨው” (Iodized edible salt) ማለት በቀጥታ ለሰው ምግብነት አገልግሎት እንዲሆን ወይም ለምግብ አምራች ፋብሪካዎች ግብዓት እንዲሆን አግባብ ባለው አካል በሚወስነው መመዘኛ መሰረት ጨው ከአዮዲን በመደባለቅ የተዘጋጀ ጨው ነው፡፡
2) “አዮዲን ያለው የገበታ ጨው” (Iodized table salt) ማለት በቀጥታ ለሰው ምግብነት አገልግሎት የሚውል አግባብ ባለው አካል በሚወስነው መመዘኛ መሰረት ከአዮዲን ጋር በመደባለቅ የተዘጋጀ ጨው ነው፡፡
3) “ለፋብሪካ ግብአትነት የሚውል አዮዲን ያለው አንኳር ጨው” (Iodized common salt) ማለት ጨውን እንደግብአት ለሚጠቀሙ የምግብ አምራች ፋብሪካዎች ብቻ የሚውል አግባብ ባለው አካል በሚወስነው መመዘኛ መሰረት ከአዮዲን ጋር በመደባለቅ የተዘጋጀ ጨው ነው፡፡
4) “አዮዲን የሌለው ጨው” ማለት ለሰው ምግብነት አገልግሎት የማይውሉ ምርቶችን ለማዘጋጀት ወይም ለማምረት የሚያገለግል ጨው ነው፡፡
5) “ድርጅት” ማለት በምግብ ጨው ማምረት፤ ማስመጣት፣ መላክ ወይም ጅምላ ማከፋፈል እንዲሁም በድጋሜ ማሸግ ስራ ላይ የተሰማራ ተቋም ነው፡፡
6) “በድጋሜ ማሸግ” ማለት መስፈርቱን ካሟላ ፋብሪካ አዮዲን የተደባለቀበትን ጨው ወስዶ በራሱ አርማ እና የንግድ ስም ጨውን መልሶ በማሸግ ስራ ላይ የተሰማራ ተቋም ነው፡፡

7) “የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት” ማለት በምግብ ጨው ማምረት፤ ማስመጣት፣ መላክ ወይም ጅምላ ማከፋፈል እንዲሁም በድጋሜ ማሸግ ስራ ላይ የተሰማራ ድርጅት አስፈላጊውን መስፈርት አሟልቶ ሲገኝ በባለሥልጣኑ የሚሰጥ የሥራ ፈቃድ ነዉ፡፡
8) “አስፈላጊ ዶክመንቶች” ማለት ጨው የተቀመጠለትን አስገዳጅ የጥራት እና የደህንነት ደረጃ እንደሚያሟላ የሚያረጋግጡ፤ ማን ምን እንደሚሠራ፤ መቼ እና እንዴት እንደሚሠራ የሚገልፁ በፅሁፍ የተቀመጡ መመሪያዎች፤ ማንዋሎች ወይም ሠንጠረዦች ናቸው፡፡
9) “የጤና ምስክር ወረቀት” ማለት እንደቅደም ተከተሉ ወደ አገር ውስጥ ለሚገባ ወይም ወደ ውጪ አገር ለሚላክ የምግብ ጨው አግባብ ካለው የውጪ አገር ወይም የሀገር ውስጥ አካል ወይም በባለሥልጣኑ ጨው ለሰው ምግብነት የሚውል መሆኑን ለማረጋገጥ የሚሰጥ ሰነድ ነው፡፡
10) “ባለስልጣን” ማለት የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፡፡
11) “ባለሙያ” ማለት የምግብ ጨው ንግድ ድርጅት በሚያስመጣው ወይም በሚልከው ወይም በሚያከፋፍለው ጨው ደህንነትና ጥራት ጋር በተያያዘ ሁኔታ የሚሰራ ማንኛውንም ስራ በበላይነት የሚመራና የሚቆጣጠር ሰው ነው፡፡
12) “አዋጅ” ማለት የምግብና መድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011 ነው፡፡
13) “ደንብ” ማለት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በቁጥር 204/2003 የጸደቀውን ጨውን በአዮዲን የማበልጸግ ደንብ ነው፡፡
14) “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡
15) ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸ አገላለጽ ሴትንም ይጨምራል፡፡

## 4. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ

1) ለሰው ምግብነት እና ለምግብ ፋብሪካ ግብአትነት በሚውል የጨው ምርት፤እና
2) በምግብ ጨው ማምረት፣ በድጋሜ ማሸግ፣ መላክ፣ ማስመጣትና ጅምላ ማከፋፈል ስራ ላይ በተሰማሩ ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## ስለ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እና የገበያ ፈቃድ

### 5. ስለ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አስፈላጊነት

1) ማንኛውም ሰዉ ከባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳያገኝ በምግብ ጨው ማምረት፣ በድጋሜ ማሸግ፣ መላክ፣ ማስመጣት ወይም ማከፋፈል ንግድ ሥራ ላይ መሰማራት አይችልም፡፡
2) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያመለክት ማንኛውም ሰው በክፍል ሶስትና አራት ስር የተጠቀሱትን አስፈላጊ መስፈርቶች ካሟላ በኂላ በአዝል አንድ (አዝል 1) ስር ከሚገኘው ማመልከቻ ቅፅ በመሙላት ለባለሥልጣኑ ማመልከት አለበት፡፡
3) ማመልከቻዉ የተሟላ ከሆነ ባለሥልጣኑ ከሁለት አባላት ባላነሰ የተቆጣጣሪ ቡድን ድርጅቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ያለክፍያ እንዲታይ ያደርጋል፡፡
4) ድርጅቱ አስፈላጊውን መስፈርት ማሟላቱ ከተረጋገጠና የአገልግሎት ክፍያ ከከፈለ በኃላ ባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አዘጋጅቶ መስጠት አለበት (አዝል 2 እና 3) ፡፡
5) በበማንኛውም ጊዜ  የኢንስፔክሽን ሪፖርቱ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 7 ላይ የተዘረዘሩትን መሰረታዊ ሁኔታዎች ሲሟሉ ባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል ፡፡ ሆኖም ግን ድርጅቱ ማሟላት ያለበትን ሁኔታዎች እንዲያሟላ በፅሁፍ ተነግሮት ሳያሟላ ሲቀር ተገቢዉን ክፍያ ሲከፍል በድጋሜ ሊታይለት ይችላል፡፡

### 6. ስለ ነጥብ አሰጣጥ ሂደት

1) የዚህ መመሪያ አንቀፅ (5) እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የምግብ ጨው አምራች  የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት በመመሪያው ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች ቢያንስ 85% ማሟላት አለበት፡፡

2) የዚህ መመሪያ አንቀፅ (5) እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የምግብ ጨው አስመጪ ወይም አከፋፋይ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት በመመሪያው ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች ቢያንስ 75% ማሟላት አለበት፡፡

## 7. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

1) ማንኛውም በምግብ ጨው ማምረት ወይም በድጋሜ ማሸግ ስራ ላይ የተሰማራ ድርጅት በዚህ መመሪያ ላይ የተቀመጡት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሁኖ ከሚከተሉት መስፈርቶች ውስጥ አንዱን ካላሟላ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ አይሰጠውም::

   ሀ) የጥሬ እቃ ማከማቻ ክፍል/ቦታ እና የጨው ማበልፀጊያ ውህዶች ማከማቻ ፤

   ለ) የማምረቻና አዮዲን ያለው ጨው ማከማቻ ቦታ ህንፃው ወለልና ግድግዳ ለማፅዳት ምቹ የሆነ፤

   ሐ) ጨው ለማምረትና በአዮዲን ለማበልጸግ የሚያስችሉ የማምረቻ መሳሪያዎች ሲያሟላ ወይም በድጋሜ ማሸግ ስራ ላይ የተሰማራ ከሆነ የሚረከበውን አዮዳይዝድ ጨው በድጋሜ ለማሸግ የሚያገለግሉ መሳሪያዎች ሲያሟላ

   መ) በጨዉ ውስጥ ያለው የአዮዲን መጠን እንዳይባክን ለመጠበቅ የሚያስችል በቂ የአየር ዝውውር ያለው የማምረቻና ማከማቻ ቦታ ከሌለው፤ ወይም እንደአካባቢው ሁኔታ በጨዉ ውስጥ ያለው የአዮዲን መጠን እንዳይባክን ለመጠበቅ የሚያስችል ቬንትሌተር ወይም ኤርኮንዲሽነር ወይም የአየር ማቀዝቀዣ ሲያሟላ፤

   ሠ) የድርጅቱ መልካም አመራረት ስርአት ወይም አሰራር መመሪያዎች፤

   ረ) ቴክኒካል ባለሞያዎች ሲያሟላ

   ሰ) መሰረታዊ የጥራት መመርመሪያ መሳሪያዎች ሲኖሩት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡፤

2) የዚህ አንቀጽ ንኡስ-አንቀጽ (1)ድንጋጌ ቢኖርም ማንኛውም የምግብ ጨው አምራች በምግብ አምራች ቅድመ-ፈቃድ መመሪያ የተደነገጉ የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች ማሟላት አለበት

## 8. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለ ማይጠየቅባቸው ሁኔታዎች

ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳያስፈልግ የምግብ ጨው ወደ አገር ዉስጥ ለማስገባት ወይም የሚቻለዉ ምርቱ

1) ለግለሰብ ጠቀሜታ፤
2) ለሳይንሳዊ ምርምር አገልገሎት፤ እና
3) ለሰብዓዊ እርዳታ አገልግሎት፤ የሚውል ሲሆን ብቻ ነው፡፡

## 9. የአድራሻና የባለቤትነት ለውጥ ስለማድረግ

ማንኛውም የምግብ ጨው ንግድ ድርጅት ባለስልጣኑን ሳያስፈቅድ ድርጅቱ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ካገኘበት አድራሻ ወደ ሌላ አድራሻ ማዛወር ወይም የባለቤትነት ለውጥ ማድረግ እንዲሁም የቴክኒካል ሃላፊ ለውጥ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

## 10. ምትክ ስለ ማግኘት

ድርጅቱ የተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተበላሸበት ወይም የጠፋበት ከሆነ ምትክ ሊያገኝ የሚችለው ቀጥሎ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ሲያሟላ ይሆናል፡፡

1) ድርጅቱ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የተበላሸበት ከሆነ የተበላሸዉን የምስክር ወረቀት ሲመልስ፤
2) ድርጅቱ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የጠፋበት ከሆነ፤ የጠፋበት ስለመሆኑ የሚገልፅ ከፍትህ አካል ማረጋገጫ ሲያቀርብ እና
3) አስፈላጊውን የአገልግሎት ክፍያ ሲከፍል ነው፡፡

## 11. ስለ እድሳት

1) ማንኛዉም ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ሊታደስለት የሚችለዉ የምስክር ወረቀቱ ካልታገደ፣ ካልተሰረዘ ወይም ድርጅቱ በራሱ ፈቃድ ስራዉን ካላቋረጠ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በሚያወጣው የጊዜ ገደብ ብቻ ይሆናል፡፡

2) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የሚታደሰው አስፈላጊ መመዘኛዎች መሟላታቸው በባለስልጣኑ ተቆጣጣሪዎች በዓመታዊ ኢንስፔክሽን ሲረጋገጥ ብቻ ይሆናል፡፡
3) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (3) መሠረት ሳይታደስ ከቀረ እንደተሰረዘ ይቆጠራል፡፡

**12. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አቀማመጥ**

ማንኛውም ድርጅት የተሰጠውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ዋና ቅጂ ሁልጊዜ በግልፅ እና በሚታይ ቦታ ማሰቀመጥ አለበት፡፡

**13. ስለ ምዝገባና ገበያ ፈቃድ**

ማንኛውም የምግብ ጨው ማምረት ወይም እንደገና ማሸግ ስራ ላይ የተሰማራ ድርጅት ምርቱን ሳያስመዘግብና የገበያ ፈቃድ ሳያገኝ ለንግድ ወይም ህብረተሰብ አገልግሎት ማቅረብ አይችልም፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለ ማምረቻና ማከማቻ ህንፃ አሰራርና አስፈላጊ መሳሪያዎች

**13. ስለ ህንፃ አሰራር ሁኔታ**

ማንኛውም የምግብ ጨው አምራች ወይም ድጋሜ ማሸግ ስራ ላይ የተሰማራ ድርጅት የምግብ ጨዉን ለማምረት የሚውለው (የሚጠቀምበት) ህንፃ የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡

1) **ስለ ማምረቻ ህንፃ**

ማንኛውም የምግብ ጨው አምራች ወይም ድጋሚ ማሸግ ላይ የተሰማራ ድርጅት፤

ሀ) ማምረቻ ወይም ድጋሚ አሻጊ ድርጅቱ የሚቋቋምበት አካባቢ ለምግብ ጨው ማምረት አገልግሎት ምቹ በሆነ ቦታ፣ የምግብ ጨው ሊበክሉ ለሚችሉ ነገሮች ተጋላጭ ያልሆነና የመሰረተ ልማት አውታሮች የተሟላለት መሆን አለበት፡፡

ለ) የህንፃው አሰራር የሚመረተውን የምግብ ጨው ለብክለት የማያጋልጥና በምርቱ ጥራት ላይ ተፅእኖ በማያሳድር መልኩ የተገነባ መሆን አለበት፡፡

ሐ) ህንፃው የተገነባበት ግብአት ከድንጋይ፣ ብሎኬት፣ ሸክላ ወይም ሌሎች ሙቀት አምቀው ከማይዙና በክፍሉ ሙቀት ላይ ተፅእኖ ከማያሳድሩ ቁሳቁስ የተገነባ መሆን አለበት፡፡

መ) የህንፃው ስፋት እንደሚያመርተው መጠን በቂ ሆኖ ቢያንስ የጥሬ እቃ፣ ምርትና የማበልፀጊያ ውሁዶች ማከማቻ፣ ጨውን በአዮዲን አዘል ውህድ ማደባለቂያ፣ የጥራት ቁጥጥር ላቦራቶሪ፣ ጥቅም ላይ የማይውል ጨው ማቆያ በቂ ቦታ፣ መፀዳጃ ቤት፣ የእጅ መታጠቢያና ሻወር ቤት ሊኖረው ይገባል፡፡

ሠ) ግድግዳው በቀላሉ ሊፀዳ የሚችል መሆን አለበት፡፡

ረ) ወለሉ በሴሚንቶ ኮንክሪት ወይም ሌላ ተመሳሳይ ማቴሪያል የተሰራ ሆኖ የማያዳልጥ፣ በቀላሉ ሊፀዳ የሚችልና ውሀ የማያቁር መሆን አለበት፡፡

ሰ) የህንፃው በርና መስኮት የምግብ ጨዉን ሊበክሉ ከሚችሉ አቧራ፣ ዝናብ፣ ቀጥተኛ የፀሀይ ብርሃንና ሌሎች በካይ ነገሮችን የማያስገባ መሆን አለበት፡፡

ሸ) የህንፃው ብርሃን ሰጪ አምፖሎች በድንገት ቢሰበሩ የምግብ ጨውን እንዳይበክሉ መሸፈን አለባቸው፡፡

ቀ) የክፍሉ ጣሪያ ሙቀት ሊቀንስ ከሚችል ማቴሪያል የተሰራ ሆኖ ቀጥተኛ የፀሀይ ብርሃንና ዝናብ የማያስገባ መሆን አለበት፡፡

በ) ክፍሉ በቂ ብርሃንና የአየር ዝውውር ሊኖረው ይገባል፡፡

2) **ስለ ማከማቻ ህንፃ**

ማንኛውም የምግብ ጨው ለማከማቸት የሚውል ህንፃ ቦታ ሁኔታ የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡

ሀ) የሚከማቸውን የምግብ ጨው ለብክለትና ለአዮዲን ብክነት የማያጋልጥና በጥራቱ ላይ ተፅእኖ በማያሳድር መልኩ የተገነባ መሆን አለበት፤

ለ) የተገነባበት ግብአት ከድንጋይ፣ ከብሎኬት፣ ከሸክላ ወይም ሌሎች በክፍሉ ሙቀት ላይ ተፅእኖ ሊያሳድሩ ከማይችሉ ነገሮች የተሰራ መሆን አለበት፤

ሐ) ስፋቱ እንደሚያከማቸው የምግብ ጨው መጠን በቂ ሆኖ ቢያንስ የማከማቻ ክፍል እና ጥቅም ላይ የማይውል ጨው ማቆያ የተከለለ ቦታ ወይም የተለየ ቦታ ሊኖረው ይገባል፤

መ) በርና መስኮቱ ነፍሳት፣ ቆርጣሚ እንስሳትና ሌሎች ጨዉን ሊበክሉ ከሚችሉ በካይ ነገሮች በማያስገባ መልኩ የተገነባ መሆን አለበት፤

ሠ) ወለሉ በሴሚንቶ፣ ኮንክሪት፣ ሴራሚክ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ማቴሪያል የተሰራ ሆኖ በቀላሉ ሊፀዳ የሚችልና ውሀ በማያቆር መልኩ የተሰራ መሆን አለበት፤

ረ) ግድግዳው በቀላሉ ሊፀዳ የሚችልና ልሙጥ መሆን አለበት፤

ሰ) የክፍሉ ጣሪያ ሙቀት ሊቀንስ ከሚችል ማቴሪያል የተሰራ ሆኖ ቀጥተኛ የፀሐይ ብርሃንና ዝናብ የማያስገባ መሆን አለበት፤

ሸ) በቂ ብርሀንና የአየር ዝውውር ሊኖረው ይገባል፡፡

## 14. ስለ አስፈላጊ መሳሪያዎችና ግብአቶች

1) **የምግብ ጨው ማምረቻ ድርጅት** ማንኛውም የምግብ ጨው አምራች ወይም ጨውን በድጋሜ ማሸግ ስራ ላይ የተሰማራ ድርጅት ጨዉን ለማምረት የሚያስፈልጉ የሚከተሉት መሳሪያዎችና ግብአቶች ሊኖሩት ይገባል፡፡

ሀ) አምራች ድርጅቱ የጨዉን ጥራት መጠበቅ የሚያስችሉ የጨው ማጣሪያ፣ ጨውን በአዮዲን አዘል ውህድ ማደባለቂያ መሳሪያዎች ሊኖሩት ይገባል፤

ለ) ጨውን በድጋሜ ማምረት ስራ ላይ የተሰማራ ድርጅት ከሆነ ደግሞ ጨዉን በድጋሜ ለማሸግ የሚያስችል መሳሪያዎች ሊኖሩት ይገባል፤

ሐ) ጨውን በአስገዳጅ ደረጃው ላይ በተቀመተው የድቀት መጠን የሚፈጭ መሳሪያ፤ የጨውን የድቀት መጠን የሚለይ ወንፊት፤ ማሸጊያና የጥራት ምርመራ ለመካሄድ የሚያስፈልጉ መሰረታዊ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች ሊኖሩት ይገባል፤

መ) ከምርት ሂደቱ ጋር ቀጥተኛ ንክኪ ያላቸው ማናቸውም መሳሪያዎችና ማሽኖች ከዝገት የፀዱና ከስቴንለስ ስቲል ወይም ጨዉን ከማይበክል ማቴሪያል (Food grade) የተሰሩ መሆን አለባቸው፤

መ) እንደአካባቢው ሁኔታ በጨዉ ውስጥ ያለው የአዮዲን መጠን እንዳይባክን ለመጠበቅ (ለመከላከል) የሚያስችል የቅዝቃዜ ሰንሰለት መጠበቂያ ቬንትሌተር ወይም አየር ኮንዲሽነር ሊኖረው ይገባል፤

ሠ) ጨዉ የተመረተበት፣ የመጠቀሚያ ጊዜና የምርት መለያ ቁጥር እንዲሁም ሌሎች በማሸጊያ ላይ እንዲኖሩ የሚያስገድዱ መልዕክቶችን ለማተም ወይም ለመፃፍ የሚያስችል መሳሪያ ሊኖረው ይገባል፤

ረ) የድርጅቱ መልካም አመራረት ስርዓት፤የአመራረት ሂደት ፍሰትን (Product Flow Diagram) ፣ የጨዉ ጥራት ላቦራቶሪ ቁጥጥር ስርዓት፣የፅዳትና ንፅህና አጠባበቅ ሂደትና የስርጭት ስርአት መከታተያ ማንዋሎች፣አሰራር ስርአትና መመዝገቢያ ፎርማቶች (Standard Operating Procedures and recording formats) ሊኖሩት ይገባል፤

ሰ) የሰራተኞች የደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁስ እንደ ጋዎን፣ ጌንት፣ ማስክ፣ ቱታና ጫማ የመሳሰሉት ሊኖረው ይገባል፤

ረ) በቂ የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ እቋ (ቦታ) ሊኖረው ይገባል።

2) **የምግብ ጨው ላኪ፣ አስመጪ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት**

ማንኛውም የምግብ ጨው ላኪ፣ አስመጪ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት ጨዉን ለማከማቸት የሚያስፈልጉ የሚከተሉት ግብአቶች ሊኖሩት ይገባል።

ሀ) እንደአከባቢው ሁኔታ በጨዉ ውስጥ ያለው የአዮዲን መጠን እንዳይባክን ለመጠበቅ (ለመከላከል) የሚያስችል የቅዝቃዜ ሰንሰለት መጠበቂያ ቬንትሌተር ወይም አየር ኮንዲሽነር፤

ለ) የስርጭት ሰንሰለት መቆጣጠሪያ ስርዐት፤

ሐ) የሚያሰራጨውን ጨው አስገዳጅ ደረጃውን ማሟላቱን ማረጋገጫ ስርዐት፤

መ) ጥቅም ላይ የማይውል ምርት ለይቶ ማቆያ ቦታ፤

ሰ) እንደየስራ ባህሪው የሰራተኞች የግል ደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁሶች (ማቴሪያሎች)።

# ክፍል አራት

# ስለ ቴክኒካል ባለሞያዎች፣ የሞያ ክህሎት እና ጤንነት

## 15. ስለ ቴክኒካል ባለሞያ

1) በማንኛውም የምግብ ጨው ማምረቻ ድርጅት ውስጥ የምርት ክፍል ሀላፊ ሆኖ የሚሰራ ባለሞያ በምግብ ሳይንስና ድህረ ምርት ቴክኖሎጂ፣ በምግብ ቴክኖሎጂ፣ በምግብ ሳይንስና ኑትሪሽን፣ በምግብ ሀይጅን፣ በምግብ ኢንጅነሪንግ፣ በአፕላይድ ኬሚስትሪ፣ በኢንዳስትሪያል ኬሚስትሪ፣ በአፕላይድ ባዮሎጂ ወይም ከነዚህ ሞያዎች ተመሳሳይ በሆኑ ሞያዎች የተመረቀ ሁኖ ለዲፕሎማ 2 ዓመት፣ ለዲግሪ ዜሮ ዓመት ወይም ከዛ በላይ የስራ ልምድ ያለው መሆን አለበት፡፡
2) ማንኛውም የምግበ ጨው ማምረቻ በድርጅቱ ውስጥ የጥራት ቁጥጥር ክፍል ሀላፊ ሆኖ የሚሰራ ባለሞያ በምግብ ሳይንስና ድህረ ምርት ቴክኖሎጂ፣ በምግብ ቴክኖሎጂ፣ በምግብ ሳይንስና ኑትሪሽን፣ በአፕላይድ ኬሚስትሪ፣ በኢንዱስትሪያል ወይም ከነዚህ ሞያዎች ጋር ተመሳሳይ በሆኑ ሞያዎች የተመረቀ ሁኖ ለዲፕሎማ 2 ዓመት፣ ለዲግሪ ዜሮ ዓመት ወይም ከዛ በላይ በምግብ ጥራት ቁጥጥር ስራ ተዛማጅ የስራ ልምድ ያለው መሆን አለበት፡፡
3) በማንኛውም የምግብ ጨው በድጋሚ ስለ ማሸግ (ማምረቻ) ድርጅት ውስጥ የምርት ክፍልና የጥራት ቁጥጥር ኃላፊ ሆኖ የሚሰራ ባለሞያ በምግብ ሳይንስና ድህረ ምርት ቴክኖሎጂ፣ በምግብ ቴክኖሎጂ፣ በምግብ ሳይንስና ኑትሪሽን፣ በምግብ ሀይጅን፣ በምግብ ኢንጅነሪንግ፣ በአፕላይድ ኬሚስትሪ፣ በኢንዳስትሪያል ኬሚስትሪ፣ በአፕላይድ ባዮሎጂ ወይም ከነዚህ ሞያዎች ተመሳሳይ በሆኑ ሞያዎች የተመረቀ ሁኖ ለዲፕሎማ 2 ዓመት፣ ለዲግሪ ዜሮ ዓመት ወይም ከዛ በላይ የስራ ልምድ ያለው መሆን አለበት፡፡

4) ማንኛውም የምግብ ጨው አስመጪ፣ ላኪ ወይም ጅምላ አከፋፋይ ድርጅትን በቴክኒካል ሀላፊነት የሚመራ ባለሞያ ቢያንስ በአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ 10ኛ ክፍል ወይም በድሮው የትምህርት ፖሊሲ 12ኛ ክፍል ያጠናቀቀ ወይም ከዚያ በላይ መሆን አለበት፡፡
5) ቴክኒካል ባለሞያው ስለ አዮዲን የበለፀገ የምግብ ጨው አመራረት፣ አያያዝ፣ አጓጓዝ፣ አከመቻቸትና አጠባበቅ ሁኔታና አሰራር እውቀት ቢኖረው ይመረጣል፡፡

## 16. ስለ ሰራተኞች ጤናና ንፅህና አጠባበቅ ሁኔታ

1) ማንኛውም ድርጅት ከምርቱ ጋር ቀጥተኛ ንክኪ ያላቸው ሠራተኞች ስራ ከመጀመራቸው በፊት በምግብ ንክኪ ከሚተላለፉ በሽታዎች ነፃ ስለመሆናቸው ማረጋገጥ አለበት፡፡
2) ሠራተኞች ስራ ከመጀመራቸውም ሆነ በስራ ላይ እያሉ ስለ መሠረታዊ አዮዲን ያለው ጨው ባህሪያት፣ አከመቻቸት፣ አያያዝና መደረግ ስላለበት ጥንቃቄ እና የመሳሰሉ ስልጠናዎች መውሰድ አለባቸው፡፡
3) ድርጅቱ በምግብ ጨው ማምረት ወይም ሽያጭ ላይ የተሠማሩ ባለሙያዎች በየስድስት ወሩ የተላላፊ በሽታ ምርመራ እንዲያካሂዱ የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡
4) ማንኛውም በምግብ ጨው ማምረት ወይም ሽያጭ ስራ ላይ የተሰማራ ሰራተኛ በስራ ጊዜ በማንኛውምተላላፊ በሽታዎች ታሞ የበሽታ ምልክቶችን እንደተቅማጥ፣ ትኩሳት፣ ትውከትና የመሳሰሉት ካለበት በሽታው እስኪድን ድረስ ከዚሁ ስራ ታግዶ መቆየት አለበት፡፡
5) የሰራተኞች የግል ንጽህና አጠባበቅ በየጊዜው ቁጥጥርና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡
6) የድርጅቱ ሰራተኞች እንደየስራው ባህሪ የስራ ደህንነት መከላከያ መሳሪያዎች ሊያደርጉ ይገባል፡፡

# ክፍል አምስት

# የምግብ ጨው ስለ ማምረት፣ በድጋሜ ማሸግ፤ ማስመጣት፣ መላክና ጅምላ ማከፋፈል

## 17. የምግብ ጨው ስለማምረት

1) ማንኛውም ድርጅት ለሰው ምግብነት እንዲሁም ለፋብሪካ ግብዐት የሚውል ጨው ማምረት እንዲሁም ወደገበያ ማቅረብ የሚችለው በኢትዮጲያ አስገዳጅ ደረጃ የተቀመጡትን መስፈርቶች ሲያሟላ ብቻ ነው፡፡
2) ማንኛውም በአዮዲን ለማበልፀግ የሚውል የምግብ ጨው ቢያንስ 98% የሶድየም ክሎራይድ (NaCl) ውሁድ መጠን እንዲሁም ለምግብ ፋብሪካዎች የሚውል አንኳር ጨው 97% የሶድየም ክሎራይድ (NaCl) ውሁድ መጠን ሊኖረው ይገባል፡፡
3) ማንኛውም አዮዲን ያለው የገበታ ጨው የእርጥበት መጠን (Moisture content) ከ 0.5% መብለጥ የለበትም፡፡
4) ማንኛውም አዮዲን ያለው ለምግብ ፋብሪካዎች የሚውል አንኳር ጨው የእርጥበት መጠን (Moisture content) ከ 3% መብለጥ የለበትም፡፡
5) ማንኛውም አዮዲን ያለው የገበታ ጨው የድቀት መጠን (Particle size) ከጠቅላላ ጨው ከ99% በላይ በአንድ ሚሊሜትር የወንፊት ቀዳዳ (sieve size) ማለፍ የሚችል፤ ከ20% በታች በ0.212 ሚሊሜትር የወንፊት ቀዳዳ ማለፍ የሚችል መሆን አለበት፡፡
6) ማንኛውም አዮዲን ያለው የገበታ ጨው ምንም አይነት ባዕድ ሽታ የሌለው እንዲሁም ሌሎች ባዕድ ነገሮች የሌሉት መሆን አለበት፡፡
7) ማንኛውም አዮዱን ያለው የገበታ ጨው ፤ 10 ግራም በ 100 ሚሊ ሊትር ውሐ በሚሟሟበት ጊዜ ምንም አይነት ቀለም የሌለው እና ኒውትራል ውህድ (Neutral solution) መፍጠር አለበት፡፡

## 18. ስለ ጨው ማበልፀጊያ ውህዶች

1) ማንኛውም ድርጅት ጨውን በአዮዲን ማበልፀግ የሚችለው በፖታሽየም አዮዴት ($KIO_3$) ፣ ፖታሽየም አዮዳይድ ($KI$)፣ ሶድየም አዮዴት ($NaIO_3$) ወይም ሶድየም አዮዳይድ ($NaI$) ውህዶችን በመጠቀም ይሆናል፡፡
2) ማንኛውም ድርጅት ጨውን በአዮዲን ለማበልፀግ ፖታሽየም አዮዳይድ ወይም ሶድየም አዮዳይድ ከተጠቀመ በጨው ውስጥ የተዋሃደው አዮዲን ተጠብቆ እንዲቆይ የሚያስችሉ ኬሚካሎችን (Stabilizers) በሀገራዊ የምግብ ጨው ደረጃ ላይ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት መጨመር አለበት፡፡
3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) ስር የተዘረዘሩት ውህዶች በባለስልጣኑ ተመዝግበው በህጋዊ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ወይም በሀገር ውስጥ የተመረቱና ጥራታቸው የተረጋገጠ መሆን አለባቸው፡፡

## 19. ስለ የአዮዲን መጠንና በካይ ነገሮች

1) ማንኛውም የምግብ ጨው በማምረት/ በድጋሜ ማሸግ ላይ የተሰማራ ድርጅት ለሰው ምግብነት የሚውል የገበታ ጨው ማቅረብ የሚችለው በአንድ ኪሎግራም የምግብ ጨው ውስጥ በማምረቻ ቦታ ላይ ከ 30- 40 ሚሊግራም አዮዲን ያለውን ጨው መሆን አለበት፡፡
2) ማንኛውም የምግብ ጨው በማምረት/ በድጋሜ ማሸግ ላይ የተሰማራ ድርጅት ለምግብ ፋብሪካዎች የሚውል አንኳር ጨው ማቅረብ የሚችለው በአንድ ኪሎግራም የምግብ ጨው ውስጥ በማምረቻ ቦታ ላይ ከ 20- 40 ሚሊግራም አዮዲን ያለውን ጨው መሆን አለበት፡፡
3) በማንኛውም የምግብ ጨው ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉ በካይ ነገሮች መጠን በሀገራዊ የምግብ ጨው ደረጃ ላይ ከተቀመጠው መጠን ማለፍ የለባቸውም፡፡

4) በምግብ ጨው ላይ የሚጨመሩ እንደ የፀረ ግግር፣ ፀረ አረፋ፣ ፀረ ሞልድና ሌሎች በጨዉ ላይ የሚጨመሩ ኬሚካሎች በሀገራዊ የምግብ ጨው ደረጃ ላይ የተቀመጠውን መስፈርት ማሟላት አለባቸው።

## 20. የምግብ ጨው ስለ ማሸግ

1) ማንኛውም የምግብ ጨው ማሸጊያ በውስጡ ያለው የአዮዲን መጠንን ሳይባክን ሊያቆይ የሚያስችል መሆን አለበት።
2) ማንኛውም ለምግብነት የሚውል አዮዲን ያለው የገበታ ጨው መታሸግ ያለበት ከ3 ኪሎ ግራም በማይበልጥ ማሸጊያ፤ ለምግብ ፋብሪካዎች ግብአት የሚሆነው አዮዲን ያለው አንኳር ጨው ደግሞ ከ50 ኪሎ ግራም በማይበልጥ ማሸጊያ መሆን አለበት።
3) ለምግብ ጨው ማሸጊያ የሚውል ከረጢት እርጥበት ወይም ውኃ የማያስገባ፣ ከቀጥተኛ የፀሀይ ብርሃንና ውጫዊ አየር የሚከላከልና በጨዉ ጥራት ላይ ተፅእኖ የማያሳድር ሆኖ ከሚከተሉት ማቴሪያሎች በአንዱ የተሰራ መሆን አለበት፤
   ሀ) ከፍተኛ ውፍረት ካለው ፖሊኢትሊን (High density polyethylene (HDPE) ፣
   ለ) ፖሊፕሮፒሊን (Polypropylene (PP) የተሸፈነ ከረጢት ወይም
   ሐ) በቃጫ ከረጢቶች የተሸፈኑ Low density polyethylene (LDPE) ወይም ሌላ በባለስልጣኑ ተቀባይነት ካገኙ ግብአቶች፤
4) እንደ ማዳበሪያ፣ ሲሚንቶ ወይም ሌላ ኬሚካል ይዞ የነበረ ወይም ቀድሞ (በፊት) ጥቅም ላይ የዋለ ከረጢት ለምግብ ጨው ማሸጊያነት መጠቀም (ማዋል) አይቻልም።

## 21. ስለ ገላጭ ፅሁፍ

1) በማንኛዉም ለምግብ የሚውል የገበታ ጨው ማሸጊያ ላይ የሚለጠፍ ወይም የሚታተም ገላጭ ፅሑፍ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ የተጻፈ ሆኖ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት□:
   ሀ) የጨዉ ንግድ ስም፤
   ለ) የአምራቹን/ አሻጊውን ስም፤
   ሐ) የተመረተበት ሀገር፤

መ) በጨው ውስጥ የሚገኙ ግብዐቶች (ingredient list) ፤

ሠ) የአምራቹ/ የአሻጊው አድራሻ፤

ረ) ምርቱ የተመረተበት ወር እና አመት፤

ሰ) የምርት መለያ ቁጥር (Batch number) ፤

ሸ) በጨው ውስጥ ያለው የአዮዲን መጠን በሚግ/ኪግ፤

ቀ) የምርቱ የአግልግሎት ጊዜ ማብቂያ፤

በ) የጨው የተጣራ ክብደት፤

ተ) ብሄራዊ አስገዳጅ ደረጃ አርማ፤

ረ) የአጠቃቀም መመሪያ፤

ሸ) ጨው በቀዝቃዛ፣ ንፁህ፣ ደረቅና ቀጥተኛ የፀሐይ ብርሃን በማይደርስበት ስፍራ ላይ መቀመጥ እንዳለበት የሚገልፅ ገላጭ ፅሁፍ□

2) በማንኛዉም ለምግብ ፋብሪካዎች የሚውል አንኳር ጨው ማሸጊያ ላይ የሚለጠፍ ወይም የሚታተም ገላጭ ፅሑፍ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ የተጻፈ ሆኖ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት።

ሀ) የጨዉ ንግድ ስም፤

ለ) የአምራቹን ስም፤

ሐ) የተመረተበት ሀገር፤

መ) የአምራቹ አድራሻ፤

ሠ) ምርቱ የተመረተበት ወር እና አመት፤

ረ) የምርት መለያ ቁጥር (Batch number) ፤

ሰ) በጨው ውስጥ ያለው የአዮዲን መጠን በሚግ/ኪግ፤

ሸ) የምርቱ የአግልግሎት ጊዜ ማብቂያ፤

ቀ) የጨው የተጣራ ክብደት፤

በ) ብሄራዊ አስገዳጅ ደረጃ አርማ፤

ተ) የአጠቃቀም መመሪያ፤

ቸ) በቀጥታ ለሰው ምግብነት የማይውል የሚል ገላጭ ፅሁፍ፤

ኀ) ለችርቻሮ ሽያጭ የማይውል የሚል ገላጭ ፅሁፍ□

3) ማንኛውም ሰው አዮዲን ባለው ጨው ማሸጊያ ላይ በጉልህ የማይታይ ፅሁፍ፣ በቀላሉ ሊጠፉ የሚችል ወይም ሌላ አሳሳች ገላጭ ፅሁፍ መጠቀም ወይም መለጠፍ የተከለከለ ነው፡፡

## 22. የምግብ ጨው ወደ ሀገር ውስጥ ስለማስገባት

1) ማንኛውም ሰው የምግብ ጨው ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት የሚችለው አዮዲን ያለው ጨው ሆኖ በዚህ መመሪያ የተቀመጡትን አግባብ ያላቸው መስፈርቶችን ሲያሟላ ይሆናል፡፡
2) ማንኛውም ሰው የምግብ ጨው ከመውጫና መግቢያ በር ላይ ለማስለቀቅ የሚከተሉትን ሰነዶች ከማመልከቻው ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

ሀ) ከኦርጅናሉ ጋር የተገናዘበ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ኮፒ፤

ለ) የጤና ሰርተፊኬት (Health certificate)፤

ሐ) የምግብ ጥራት ምርመራ ሰርተፊኬት (Certificate of analysis)፤

መ) የስሪት አገር ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (Certeficate of origin)፤

ሠ) የምርት ሽያጭ ሰርተፊኬት (Free sales Certeficate)፤

ረ) የእቃ ዝርዝር መግለጫ ሰነድ (Packing list)፤

ሰ) የግምሩክ ዲክላራስዮን (Custom declaration)፤

ሸ) ቢል ኦፍ ሎዲንግ ወይም ኤርዌይ ቢል (Bill of loading or Airway bill)፤

ቀ) ኢንቮይስ (Comercial invoice) □

## 23. የምግብ ጨው ወደ ውጭ ሀገር ስለ መላክ

ማንኛውም ሰው የምግብ ጨው ወደ ውጭ ሀገር መላክ ሲፈልግ ለሚልከው ጨው የጤና ሰርተፊኬትና ሌሎች መረጃዎች እንዲሰጠው ሲጠይቅ ባለስልጣኑ በዚህ መመሪያ የተቀመጡ መስፈርቶችን ማሟላቱን ሲያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

## 24. የምግብ ጨው ስለ ማከፋፈል

1) ማንኛውም ሰው የገበታ ጨው እንዲሁም ለምግብ ፋብሪካዎች ግብአት የሚሆን አንኳር ጨው ማከፋፈል የሚችለው ሀገራዊ አስገዳጅ ደረጃን ማሟላቱን ሲያረጋግጥ ብቻ ነው፡፡
2) ማንኛውም ሰው የገበታ ጨው እንዲሁም ለምግብ ፋብሪካዎች ግብአት የሚሆን አንኳር ጨው ማከፋፈል የሚችለው የአዮዲን ይዘቱ በአንድ ኪሎ ግራም ጨው ውስጥ ከ20- 40 ሚሊ ግራም አዮዲን ያለውን ሲሆን ብቻ ነው፡፡
3) ማንኛውም ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት የምግብ ጨው መግዛት የሚችለው ከባለስልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከተሰጠው የጨው አምራች ወይም አስመጪ ድርጅት ብቻ ነው፡፡
4) ማንኛውም ጅምላ አከፋፋይ ድርጅት የምግብ ጨው ሲሸጥ "ቀድሞ የገባውን ቀድሞ ማውጣት" /First In First Out (FIFO)/ እና "ቀድሞ የመጠቀሚያው ጊዜ የሚያበቃውን ቀድሞ ማውጣት" /First Expiry First Out (FEFO)/ በሚለው መርህ መሰረት መሆን አለበት፡፡
5) ማንኛውም ድርጅት የምግብ ጨዉ ሲገዛና ሲሸጥ የድርጅቱ ስምና ህጋዊ ማህተም ያረፈበት ደረሰኝ እንደቅደም ተከተሉ የመቀበልና የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

## 25. የምግብ ጨው ስለ ማከማቸት

1) ማንኛውም ድርጅት የምግብ ጨው ሲያከማች የጥራት ጉድለትና የአዮዲን ብክነት ሊያስከትሉ ከሚችሉ ነገሮች እንደ እርጥበትና ለቀጥተኛ የፀሐይ ብርሃን በተጋለጠ መልኩ ማከማቸት የለበትም፡፡
2) ማንኛውም ድርጅት የምግብ ጨው ሲያከማች ከማከማቻ ክፍሉ ጣሪያ 50 ሴንቲሜትር ዝቅ ብሎ እና ከግድግዳው 20 ሴንቲሜትር ርቆ ማከማቸት አለበት፡፡
3) ድርጅቱ በማከማቻው ውስጥ ቀድሞ የተመረተ ወይም የገባ ጨው ቀድሞ ለማውጣት በሚያመች መልኩ መከማቸት አለበት፡፡
4) ድርጅቱ እንደየአከባቢው ሁኔታ የማከማቻ ክፍሉ ሙቀትና እርጥበት በየጊዜው በመለካት ከሚፈለገው መጠን በላይ ሲሆን አስፈላጊውን ማስተካከያ ማድረግ አለበት፡፡

5) ማንኛውም የተበላሸ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜዉ ያለፈበት የምግብ ጨው በአግባቡ ተቆጥሮና ተመዝግቦ ጥቅም ላይ ከሚውለው የምግብ ጨው ተለይቶ ለብቻው መቀመጥ አለበት፡፡
6) ማንኛውም ድርጅት በማንኛውም ሁኔታ የምግብ ጨው አዮዲን ከሌለው ጨው ቀላቅሎ ማከማቸት ወይም ለሽያጭ ማቅረብ አይችልም፡፡

## 26. የምግብ ጨው ስለ ማጓጓዝ

ማንኛውም የምግብ ጨውን ሊበክልና በውስጡ ያለውን የአዮዲን መጠን ሊያባክን (ሊቀንስ) ከሚችል እንደ ቀጥተኛ የፀሐይ ብርሃን፣ ዝናብ፣ አቧራና ሌሎች በጨዉ ደህንነትና ጥራት ላይ ተፅእኖ ሊያሳደሩ ከሚችሉ ነገሮች በተጋለጠ መልኩ መጓጓዝ የለበትም፡፡

## 27. አዮዲን የሌለው ጨው በጥቅም ላይ ስለማዋል

1) ማንኛውም ሰው ከባለስልጣኑ ልዩ ፈቃድ (እዝል 4) ካልተሰጠው በስተቀር አዮዲን የሌለው ጨው በሀገሪቱ ውስጥ መያዝ፣ ማከማቸት፣ ማጓጓዝ ወይም ለሽያጭ ማቅረብ የተከለከለ ነው፡፡
2) ማንኛውም ድርጅት አዮዲን የሌለው ጨው በጥቅም ላይ ሊያውል የሚችለው ለኢንዱስትሪ ግብአት፣ ለምርምር ወይም ሌላ ከሰው ምግብነት አገልግሎት ውጪ ለሆነ ዓላማ ሆኖ የሚያስፈልገው የጨው መጠን ለባለስልጣኑ አቅርቦ ሲፈቀድ (ፍቃድ ሲያገኝ) ብቻ ነው፡፡
3) ማንኛውም ሰው አዮዲን የሌለው ጨው ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ከባለስልጣኑ ልዩ የመግቢያ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡
4) ማንኛውም ድርጅት የሚያመርተው ጨው አዮዲን የሌለው ከሆነ "ለሰው ምግብነት አይውልም" ወይም "ለ_____አገልግሎት ብቻ" የሚል በጉልህ የተፃፈ ገላጭ ፅሑፍ በማሸጊያው ላይ መግለፅ አለበት

# ክፍል ሰባት

# አስተዳዳራዊ እርምጃዎች

## 31. ማስጠንቀቂያ ስለ መስጠት

1) ማንኛውም ድርጅት የፈፀመው ጥፋት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሚያሳግድ ወይም የሚያሰርዝ ካልሆነ በስተቀር ባለስልጣኑ እንደአግባብነቱ የቃል ወይም የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው ይችላል፡፡
2) ባለስልጣኑ ድርጅቱ በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሰረት አስፈላጊውን ማስተካከያ ካላደረገ ድርጅቱ ሊታገድ ይችላል፡፡

## 32. ስለ እገዳ

1) ማንኛዉም ድርጅት ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ባለስልጣኑ ከ 1 ወር እስከ 6 ወራት ለሚደርስ ጊዜ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ሊያግድበት ይችላል፡፡

ሀ) ሕጋዊና ወቅታዊ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከሌለው ድርጅት የምግብ ጨው ከገዛ ወይም በማንኛውም መንገድ ከተቀበለ ወይም ፈቃድ ለሌለው አከፋፋይ ድርጅት ከሸጠ፤

ለ) ባለስልጣኑን ሳያስፈቅድ በተቋሙ የቦታ አድራሻ ላይ ለዉጥ ካደረገ፤

ሐ) ከተጠቀሰው ቴከኒክ ባለሙያ እውቅና ውጪ የምግብ ጨው ሲያመርት፣ ሲያስመጣ፣ ሲልክ፣ ሲያከፋፍል ወይም ሲሸጥ፤

መ) በአእምሮ ህመም ወይም ስራውን ለማከናወን በማያስችል የአካል ጉድለት ወይም የአልኮል መጠጥ፤አደንዛዥ ዕፆች፤ የናርኮቲክ እና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን ወይም ሌላ በመውሰድ በሚነሳ የአዕምሮ ሁከት ምክንያት ወይም በዕድሜ መግፋት ምክንያት ተግባሩን በአግባቡ ማካሄድ የማይችል ባለሞያ ሲያሰራ፤

ሠ) እንደአከባቢው ሁኔታ በጨዉ ውስጥ ያለውን አዮዲን ከብክነት ለመከላከል የሚያስችል የቅዝቃዜ ሰንሰለት መጠበቂያ ቬንትሌተር ወይም አየር ኮንድሽነር ሳይኖረው ጨው ሲያመርት፣ ሲያከማች ወይም ሲያጓጓዝ፤

ሸ) ባለሥልጣኑ በድርጅቱ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ለሚያደርጋቸው ማንኛውም የኢንስፔክሽን ስራዎች እንዳያከናውን እንቅፋት የፈጠረ እንደሆነ፤

ቀ) በዚህ መመሪያ አንቀፅ (7) ስር ከተጠቀሱት መስፈርቶች መካከል አንዱን ሲያጓድል፤

በ) ድርጅቱ ከሁለት ጊዜ በላይ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ጉድለቱን የማያስተካክል ከሆነ ወይም

ተ) ከነዚህ ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸው ጥፋቶችን ፈፅሞ ሲገኝና የበላይ ሃላፊ ሲያፀድቃቸው፤

2) ማንኛውም ድርጅት አግባብ ባለው አካል በንግድ ስራ ላይ እንዳይቀጥል ከታገደ፤

## 33. ስለ ስረዛ

1) ማንኛዉም ድርጅት ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ባለስልጣኑ ቢያንስ ለ1 ዓመት ለሚደርስ ጊዜ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ሊሰረዝበት ይችላል፡፡

ሀ) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የተገኘው በማጭበርበር መሆኑ ከተረጋገጠ፤

ለ) የብቃት ማረጋገጫው ምስክር ወረቀቱ በማናቸውም መንገድ ለሌላ ሶስተኛ ወገን ካስተላለፈ፤

ሐ) ማንኛውንም የምግብ ጨው መጀመሪያ በአምራቹ ድርጅት ከተሰራ ወይም ከነበረው የሚዛን ክብደት ለመጨመር፣ መልክ ለማሳመር፣ ወይም ለሌላ ተግባር ባዕድ ነገር ጨምሮ ሲገኝ፤

መ) የተበላሸ፣ የአገልግሎት ዘመን ያለፈበት፤ ገበያ ላይ እንዳይውል የታገደ፤ አዮዲን የሌለው፣ ስለምርቱ ሁኔታ ገላጭ ፅሁፍ የሌለዉ ወይም አሳሳች ገላጭ ፅሁፍ ያለው የምግብ ጨው የያዘ፣ የሸጠ ወይም ያከፋፈለ ወይም የምግብ ጨው የከለሰ፤ አመሳስሎ ያቀረበ፣ በህገ ወጥ መንገድ የምግብ ጨው የያዘ ወይም ይህንን ስራ መከናወኑን አውቆ የምግብ ጨዉን ከያዘ፣ ከሸጠ ወይም ካከፋፈለ፤

ሠ) የማምረት ፈቃድ ሳይኖረው የምግብ ጨው እንደገና ያሸገ ወይም ሌላ ገላጭ ፅሁፍ በመለጠፍ ከሸጠ፤

ሽ) በአንቀጽ (11) መሰረት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ በወቅቱ ካልታደሰ፤

ቀ) ድርጅቱ ስለ እገዳ የተመለከተውን በአንቀፅ (30) ላይ የተቀመጡትን ተመሳሳይ ጥፋቶች ከሁለት ጊዜ በላይ ፈፅሞ ሲገኝ ወይም ድርጅቱ በባለስልጣኑ የተጣለበትን እገዳ በመተላለፍ ስራውን ከቀጠለ፤

በ) ከህብረተሰብ ጤና ቁጥጥር አንጻር ባለስልጣኑ አስፈላጊ እና ምክንያታዊ ነው ብሎ ያመነባቸውንና የበላይ ሀላፊ ያጸደቃቸዉ ሌሎች ተመሳሳይ ጥፋቶች ሲፈፅም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ሊሰርዝበት ይችላል፡፡

2) አግባብ ባለው አካል በንግድ ስራ ላይ እንዳይቀጥል ፈቃዱ ሲሰረዝ ወይም የንግድ ስራውን በራሱ ፈቃድ ሲያቋርጥ፡፡

## 34. የምግብ ጨውን ስለ መያዝ

1) ባለስልጣኑ ማንኛውም የምግብ ጨዉን ጥራትና ደህንነት ጉድለት መኖሩን ጥርጣሬ ሲኖረው ወይም በህብረተሰቡ ጤና ላይ አደጋ ሊያደርስ ይችላል ብሎ ሲያምን የምግብ ጨዉን ጥራትና ደህንነት እስኪረጋገጥ ድረስ ለብቻው ተገልሎ እንዲቆይ ሊያደርግ ይችላል፡፡
2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት ተገልሎ የተያዘ የምግብ ጨው አስፈላጊውን ምርመራ ተደርጎበት በጥቅም ላይ የማይውል መሆኑ ከተረጋገጠ ተይዞ ሊወገድ ወይም ወደ መጣበት ሀገር ሊመለስ ይችላል፡፡

## 35. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለ መመለስ

1) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ዓይነት፣ የቦታ ለውጥ ሲያደርግና አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ጠይቆ ተቀባይነት ሲያገኝ መመለስ አለበት፡፡
2) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ከተሰረዘ፣ ከታገደ፣ በተቀመጠው የእድሳት ጊዜ ገደብ ሳይታደስ ከቀረ ወይም በራሱ ፈቃድ ስራውን ካቋረጠ በሁለት የስራ ቀናት ውስጥ መመለስ አለበት፡፡

### 36. እገዳና ስረዛ ስለማንሳት

ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ድርጅት የተጣለበት እገዳ ወይም ስረዛ ሊነሳለት የሚችለው በዚህ መመሪያ መሰረት ቅሬታ አቅርቦ ቅሬታው ተቀባይነት ሲያገኝ ወይም ድርጅቱ ለእገዳ ወይም ለስረዛ ያበቃውን ጥፋት የተሰጠው የጊዜ ገደብ ሲያጠናቅቅ ባለስልጣኑ እገዳውን ወይም ስረዛውን ሊያነሳለት ይችላል፡፡

### 37. የምግብ ጨው ለሌላ አካል ስለማስተላለፍ

ማንኛውም ስራውን በራሱ ፈቃድ ያቋረጠ፣ እገዳ ወይም ስረዛ የተጣለበት ድርጅት በእጁ የሚገኘውን ጥቅም ላይ መዋል የሚችል የምግብ ጨው በባለስልጣኑ ፈቃድ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ላላቸው ሌሎች ድርጅቶች ማስተላለፍ ይችላል፡፡

### 38. የምግብ ጨው ከገበያ ላይ ስለ መሰብሰብ /Product recall/

1) ማንኛውም ድርጅት ያመረተው ወይም ያሰራጨውን የምግብ ጨው ጥራት ጥርጣሬ ውስጥ የሚያስገባ ጠቋሚ ነገሮች መኖራቸውን ሲያረጋግጥ ማንኛውም ዓይነት ሽያጭ እንዳይከናወን የማሳወቅና የማስቆም ግዴታ አለበት፡፡
2) ማንኛውም ድርጅት ያመረተውን፣ ያስመጣውን፣ የላከውን ወይም ያከፋፈለውን የምግብ ጨው የጥራትና ደህንነት ጉድለት ኖሮት ለህብረተሰቡ ጤና ጎጂ መሆኑ ሲረጋገጥ ከገበያ የመሰብሰብና ለባለስልጣኑ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡
3) ድርጅቱ በምግብ ጨዉ ብልሽት ምክንያት በህብረተሰብ ጤና ላይ ለደረሰ ችግር አግባብ ባላቸው ህጎች ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 39. የተበላሸ ወይም ተፈላጊውን ደረጃ ስለ ማያሟላ የምግብ ጨው

1) ማንኛውም ድርጅት በተለያዩ ምክንያቶች የተበላሸ፣ የአገልግሎት ጊዜው ያለፈበትና ተፈላጊውን ደረጃ የማያሟላ የምግብ ጨው ለይቶ የመያዝና ዝርዝራቸውን ለባለስልጣኑ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡
2) አስገዳጅ ሆኖ የተቀመጠውን ሀገራዊ ደረጃ የማያሟላ ጨውን በኢንስፔክሽን ወቅት የተገኘ ከሆነ ጨውን የያዘው ድርጅት አስፈላጊው አስተዳዳራዊ እርምጃ ተወስዶበት ጨዉን በባለስልጣኑ ፈቃድ እንደአግባቡ ተመልሶ በድጋሜ ሊመረት፣ ሊወገድ ወይም ከሰው ምግብነት ውጪ ዓላማ ሊውል ይችላል፡፡
3) የምግብ ጨዉ በተለያየ ምክንያት ለሰው ጤና ጎጂ በሆኑ እንደ ፀረ ተባይና በሌሎች አደገኛ ኬሚካሎች የተበከለ ከሆነ መወገድ አለበት፡፡
4) የምግብ ጨዉ እንዲወገድ የሚደረግ ከሆነ በባለስልጣኑ የምግብ ማስወገድ መመሪያ መሰረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

## 40. አስተዳዳራዊ እርምጃዎች አወሳሰድና ቅሬታ አቀራረብ

1) በዚህ ክፍል መሰረት የሚወሰዱ አስተዳዳራዊ እርምጃዎች በባለስልጣኑ የአስተዳዳራዊ እርምጃ አወሳሰድና ቅሬታ አቀራረብ መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡
2) ማንኛዉም ድርጅት ስለብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ፣ እድሳት፣ እገዳና ስረዛ ወይም ሌሎች ባለሥልጣኑ የሚወስዳቸዉ እርምጃዎችን በተመለከተ ቅር ከተሰኘ አቤቱታውን በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ ባለስልጣኑ ላቋቋመዉ ቅሬታ ሰሚ አካል ማቅረብ ይችላል፡፡
3) ቅሬታ የቀረበለት ቅሬታ ሰሚ አካል ቅሬታውን አጣርቶ በ30 ቀናት ውሰጥ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፡፡

# ክፍል ስምንት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 41. መረጃ ስለ መያዝ

1) ማንኛዉም ድርጅት ስለ አስመጣው፣ ስለ አከፋፈለው፣ ስለ ላካዉ፣ ስለተበላሸ፣ የመጠቀሚያ ጊዜዉ ስለአለፈበት፤ ስለተወገደ ጨውና ሌሎች ተያያዥ የሆኑ ሰነዶችን በአግባቡ የመያዝና በባለስልጣኑ ሲጠየቅም የማሳየት ግዴታ አለበት፡፡
2) በድርጅቱ ውስጥ ስላለው ሰራተኛ የትምህርት ደረጃ፣ የስራ ልምድ፣ የጤና ሁኔታና የወሰዱት ስልጠና ዓይነት የሚገልፅ ዝርዝር መረጃ የያዘ ፋይል መኖር አለበት፡፡
3) ድርጅቱ ዝርዝር ደረሰኞች፣ የክምችት መቆጣጠሪያ ስቶክ ቢን ካርዶችና ሌሎች መረጃዎች ሊኖሩት ይገባል፡፡
4) ድርጅቱ ጨዉን የገዛበትና የሸጠለትን ድርጅት ስምና ሙሉ አድራሻ፤ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ኮፒውን የሚገልፅ መረጃ መያዝ አለበት፡፡
5) ማንኛዉንም ድርጅት ከላይ የተጠቀሱትን መረጃዎች በአግባቡ የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡

## 43. የምግብ ጨው ስለ ማስተወወቅ

ማንኛዉም ድርጅት በማንኛውም የማስታወቂያ መንገድ ተጠቅሞ የምግብ ጨውን ማስተዋወቅ የሚችለው አግባብ ባለው የማስታወቂያ ህግ መሰረት ይሆናል፡፡

## 44. መረጃ ለሕዝብ ይፋ ስለ ማድረግ

1) ባለሥልጣኑ የወሰደውን ማንኛውም አስተዳዳራዊ እርምጃ በተመለከተ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና የቅሬታ አቀራረብ ጊዜ ገደብ ሲጠናቀቅ ወይም ቅሬታ ሰሚ አካሉ ጉዳዩን መርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ ሲሰጥ መረጃዎቹን ለህብረተሰቡ ይፋ ሊያደርግ ይችላል፡፡
2) ባለሥልጣኑ በማንኛውም ድርጅት ያገኛቸው የአሰራር ግድፈቶች፣ የተረጋገጡ ተጨባጭ ጥቆማዎች ሲያገኝና መረጃው ለሕብረተሰቡ ባለመነገሩ በህብረተሰቡ ጤና ላይ አደጋ

ሊያስከትል ይችላል ተብሎ ሲታመን መረጃዎቹ በማንኛውም የመገናኛ ዘዴ ይፋ ሊያደርግ ይችላል፡፡

3) ማንኛዉም ሰዉ በባለሥልጣኑ ምስጢር ተብለው ከተያዙ መረጃዎች በስተቀር ስለ ማንኛውም ድርጅት የሚፈልገውን መረጃ ማግኘት ይችላል፡፡

## 45. ስለ አግልግሎት ክፍያ

ማንኛዉም ድርጅት በባለስልጣኑ ለሚሰጠው አገልግሎት አግባብ ባለው አካል በሚወስነው የክፍያ ተመን መሰረት መክፈል ይኖርበታል፡፡

## 46. የመተባበር ግዴታ

ባለስልጣኑ ይህን መመሪያ ለማስፈፀም እንዲችል ጉዳዩ የሚመለከታቸው ማንኛውም የፌደራልና የክልል መንግሥት አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

## 47. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ዓይነት መመሪያ፣ የአሰራር ልምድ ወይም ሰርኩላር ደብዳቤ በዚህ መመሪያ ላይ በተካተቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

## 48. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ______________ ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**ሄራን ገርባ**

**የኢትዮጵያ የምግብና የመድኃኒት ባለስልጣን**

**ዋና ዳይሬክተር**

## እዝል 1

**የኢትዮጵያ የምግብና የመድኃኒት ባለልጣን**
Ethiopian Food and Drug Authority

**እዝል 1**

**ለምግብ ጨው አምራች፣ አስመጪ ወይም አከፋፋይ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት መጠየቂያ ቅጽ**

1. የአመልካች ሙሉ ስም ________________________________________
2. የአመልካቹ/ቿ በድርጅቱ ያለው ሀላፊነት ______________________________
3. የድርጅቱ ባለቤት ሙሉ ስም ___________________________________
   አድራሻ
   ክልል________________ዞን/ክ/ከተማ____________________ወረዳ______________
   ከተማ__________________ቀበሌ_________________ስ/ቁ(Office)______________
   ሞባይል__________________ኢሜል______________________________________

4. የድርጅቱ አድራሻ
   ክልል_____________________ዞን/ክ/ከተማ____________________ወረዳ_________
   ከተማ______________ቀበሌ____________ስ/ቁ (Office) _____________________
   ሞባይል__________________ኢሜል______________________________________
   የቦታው ልዩ መጠሪያ_______________________________________________

5. የድርጅቱ ዓይነት፡ አምራች ☐ አስመጭ ☐ ጅምላ አከፋፋይ ☐ ሳኪ ☐

6. የሚይዘው የጨው አይነት______________________________________________
7. የድርጅቱን የቴክኒክ ባለሞያ☐
   - ✓ ሙሉ ስም_________________________________________
   - ✓ የትምህርት ደረጃ_____________(የባለሞያው የውል ስምምነትና የትምህርት ማስረጃ ይያያዝ)
8. እኔ ______________________________የተባልኩኝ በምግብ ጨው ቁጥጥር መመሪያ የተቀመጡትን መስፈርቶች ስላሟላሁኝ ድርጅቴ ታይቶ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠኝ እጠይቃለሁ፡፡

   ፊርማ ____________________ቀን ____________

---

9. ለቢሮ ስራ ብቻ የሚያገለግል
   - ✓ ማመልከቻውን የተቀበለው ሰራተኛ ስም___________________ፊርማ_______
   - ✓ ማመልከቻውን የተቀበለበት ቀን________________ ሰአት___________

✓ የቀጠሮ ቀን_________________________ሰአት_________

Photo

**የኢትዮጵያ የምግብና የመድኃኒት ባለልጣን**
**Ethiopian Food and Drug Authority**

**እዝል 2**

## የምግብ ጨው ማምረቻ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት
## Certificate of Competence for Iodized Salt Manufacturing Organization

□□□/No____________________
□□/Date___________________

የድርጅቱ ስም_________________________የንግድ ስራ አይነት________________________________________
Name of business organization Buisness type
የሚያመርተው የምርትአይነት____________________________________________________________________
Product type

የድርጅቱ አድራሻ
Address of the organization
ክልል__________ዞን/ክ/ከተማ____________ወረዳ____________ከተማ_____________
Region Sub city/Zone Woreda City
ቀበሌ_______________የቤ/ቁጥር____________ስ/ቁጥር____________ፋክስ_____________
Kebele House no Telephone Fax

የድርጅቱ ባለቤት ሙሉ ስም ___________________________________
Ownwers full name

ድርጅቱ ባለስልጣኑ ያወጣውን መስፈርቶች ማሟላቱ ስለተረጋገጠ በምግብ ፣በመድኃኒትና በጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ 661/2002 መሰረት ይህ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ተሰጥቷል፡፡

This Certificate of Competence is issued upon fulfillment of requirements set by the Authority in accordance with Food, Medicine and Healthcare Administration and Control Proclamation No. 661/2009.

የሃላፊ ፊርማ________________ የተሰጠት ቀን__________
Signature of Authorized person Date of Issue

| | | |
|---|---|---|
| ታድሷል<br>Renewed<br>200_____E.C/201_____G.C<br>የደረሰኝ ቁጥር_________________<br>R/no<br>ፊርማ_________________<br>Signature | ታድሷል<br>Renewed<br>200_____E.C/201_____G.C<br>የደረሰኝ ቁጥር_________________<br>R/no<br>ፊርማ_________________<br>Signature | ታድሷል<br>Renewed<br>200_____E.C/201_____G.C<br>የደረሰኝ ቁጥር_________________<br>R/no<br>ፊርማ_________________<br>Signature |

ማሳሰቢያ/ Notice/

ይህ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረከት/ This certificate of competence
1. በየአመቱ ካልታደሰ እንደተሰረዘ ይቆጠራል፡፡

Shall be considered cancelled unless renewed every year.

2. ድርጅቱ አግባብ ካላቸው ህጎችና መስፈርቶች ውጭ ሲሰራ ሲገኝ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል፡፡
May be suspended or revoked if the organization is found in violation of applicable laws & standards authority.

Photo

## የኢትዮጵያ የምግብና የመድኃኒት ባለልጣን
## Ethiopian Food and Drug Authority

**<u>እዝል 3</u>**

### የምግብ ጨው ላኪ፣ አስመጪና ጅምና አከፋፋይ ንግድ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት
### <u>Certificate of Competence for Iodized Salt Export/Import/Wholesale Organization</u>

□□□ /No____________________
□□/Date___________________

የድርጅቱ ስም________________________የንግድ ስራ አይነት______________________________________
Name of business organization Buisness type
የሚያመርተው የምርትአይነት________________________________________________________________
Product type

የድርጅቱ አድራሻ
Address of the organization
ክልል__________ዞን/ክ/ከተማ____________ወረዳ____________ከተማ_____________
Region Sub city/Zone Woreda City
ቀበሌ_______________የቤ/ቁጥር___________ስ/ቁጥር___________ፋክስ____________
Kebele House no Telephone Fax

የድርጅቱ ባለቤት ሙሉ ስም ___________________________________
Ownwers full name

ድርጅቱ ባለስልጣኑ ያወጣውን መስፈርቶች ማሟላቱ ስለተረጋገጠ በምግብ ፣በመድኃኒትና በጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ 661/2002 መሰረት ይህ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ተሰጥቷል፡፡

This Certificate of Competence is issued upon fulfillment of requirements set by the Authority in accordance with Food, Medicine and Healthcare Administration and Control Proclamation No. 661/2009.

የሃላፊ ፊርማ_________________ የተሰጠት ቀን__________
Signature of Authorized person Date of Issue

| | | |
|---|---|---|
| <u>ታድሷል</u><br>Renewed<br>200_____E.C/201_____G.C<br>የደረሰኝ ቁጥር________________<br>R/no<br>ፊርማ________________<br>Signature | ታድሷል<br>Renewed<br>200_____E.C/201_____G.C<br>የደረሰኝ ቁጥር________________<br>R/no<br>ፊርማ________________<br>Signature | ታድሷል<br>Renewed<br>200_____E.C/201_____G.C<br>የደረሰኝ ቁጥር________________<br>R/no<br>ፊርማ________________<br>Signature |

<u>ማሳሰቢያ/ Notice/</u>

ይህ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረከት/ This certificate of competence
1. በየአመቱ ካልታደሰ እንደተሰረዘ ይቆጠራል፡፡

Shall be considered cancelled unless renewed every year.

2. ድርጅቱ አግባብ ካላቸው ህጎችና መስፈርቶች ውጭ ሲሰራ ሲገኝ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል፡፡
May be suspended or revoked if the organization is found in violation of applicable laws & standards authority.

**የኢትዮጵያ የምግብና የመድኃኒት ባለስልጣን**
Ethiopian Food and Drug Authority

## እዝል 4

## አዮዲን የሌለው ጨው የግዢ ፈቃድ መጠየቂያና መስጫ

### I. በድርጅቱ የሚሞላ

1. የአመልካች ሙሉ ስም________________________________
2. አመልካቹ/ቿበድርጅቱ የሚኖረው/ራት ሀላፊነት / መረጃ ይያያዝ______________________
3. የድርጅቱ ስም____________________________________________
4. የድርጅቱአድራሻ፡
   ክልል___________ዞን/ክ/ከተማ______________ወረዳ______________ከተማ_____________
   በሌ________________የቤ/ቁጥር_____________ስ/ቁጥር_____________ሞ/ቁጥር____________
   የቦታው ልዩ መጠሪያ_______________________________

5. ጨው የተፈለገበት ዓላማ_____________________________________________
6. የማከማቻ መጋዝን አድራሻ_________________________________________

| የሚፈለገው የጨው መጠን (ኪግ/ኩንታል | ጨው የሚገዛባት ቦታ/ሀገር | የጨው አምራች ድርጅት ስም | ጨው የሚገባበት መግቢያ በር | የማጓጓዣ አይነት | የሚጓጓዝበት ጊዜ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |

የአመልካቹ ስም____________________ፊርማ__________ቀን__________ማህተም

### II. በባለስልጣኑ የሚሞላ

ከላይ ስሙ የተጠቀሰው ድርጅት ለ________________________አገልግሎት የሚውል _________ኪግ/ኩንታል አዮዲን የሌለው ጨው ወደ ሀገርውስጥ እንዲያስገባ/ ከሀገር ውስጥ እንዲገዛ፣ እንዲያጓጉዝና እንዲያከማች በባለስልጣኑ "የምግብ ጨው ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር_________________" መሰረት የተፈቀደለት መሆኑን እየገለጽን ድርጅቱ እስከ_______________ባለው ቀን ውስጥ አጓጉዞ እንዲጨርስ እናሳስባለን፡፡

የፈቀደው ሀላፊ ስም__________________ፊርማ__________ቀን____________ማህተም

<u>ማሳሰቢያ</u>

ይህ የግዢ ፈቃድ፡

1. የሚያገለግለው ለአንድ ጊዜ ጭነት ብቻ ሆኖ ከላይ ለተገለጸው የጨው መጠን ብቻ ይሆናል፡፡
2. ጨው በሚጓጓዝበትና በሚከማችበት ጊዜ መለየት የለበትም፡፡
3. በ 3 ኮፒ የሚዘጋጅ ሆኖ 1ኛ ኮፒ ለድርጅቱ፣2ኛ ኮፒ ለኢንስፔክሽንና ሰርቪላንስ ዳይሬክቶሬት የሚሰጥ ሆኖ3ኛ ኮፒ ከድርጅቱ ፋይል ጋር የሚያያዝ ነው፡፡

**የኢትዮጵያ የምግብና የመድኃኒት ባለስልጣን**

Ethiopian Food and Drug Authority

## አዝል 5

## በኢንስፔክሽን ወቅት የተገኙ ክፍተቶችን ለማሟላት ከድርጅቱ ጋር የሚገባ መተማመኛ ሰነድ

1. የድርጅቱ ስም______________________________የምርት ዓይነት______________________
2. ድርጅቱ የሚገኝበት አድራሻ:
ክልል____________________ዞን/ክፍለከተማ____________ወረዳ____________ከተማ _____________ቀበሌ___________ልዩ መጠሪያ____________ስልክ ቁጥር_____________
3. የድርጅቱ ባለቤት/ ተወካይ____________________________________________________

| ተ.ቁ | በድርጅቱ ውስጥ የተገኙ ክፍተቶች | በድርጅቱ መወሰድ ያለባቸው የማስተካከያ እርምጃዎች | የጊዜ ወሰን | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |

| የኢንስፔክተሩ ስም | ፊርማ | የድርጅቱ ባለቤት /ተወካይ ስም | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 1.________________ | __________ | _________________________ | ________ |
| 2.________________ | __________ | ቀን_________________________ | |
| 3. ________________ | __________ | | |

ማሳሰቢያ

- ✓ ድርጅቱ የተቀመጠውን መስፈርት ከ 75 ፐርሰንት በላይ አሟልቶ ፍቃድ የሚሰጠው ከሆነ ጉድለቶችን ለማስተካከል ይህ የመተማመኛ ቅፅ በሶስት ኮፒ ተዘጋጅቶ 1 ኮፒ ለድርጅቱ የሚሰጥ፣ 2ኛ ኮፒ ከድርጅቱ ፋይል ጋር ይያዛል፣ 3ኛ ኮፒ ሊአንስፔክሽንና ሰረቬላንስ ዳይሬክቶሬት ለክትትል ይሰጣል፡፡

- ✓ ድርጅቱ መስፈርቱን ሳያሟላ ቀርቶ በድጋሚ ፈቃድ ለማውጣት የሚመለስ ከሆነ ይህ የመተማመኛ ቅፅ በሁለት ኮፒ ተዘጋጅቶ1ኛ ኮፒ ለድርጅቱ የሚሰጥ፣ 2ኛ ኮፒ ከድርጅቱ ፋይል ጋር ይያያዛል፡፡
- ✓ ድርጅቱ በገባው የመተማመኛ ሰነድ መሰረት ክፍተቶቹን በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ካላሟላ አግባብ ባለው ህግ መሰረት አስተዳዳራዊ እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

**የኢትዮጵያ የምግብና የመድኃኒት ባለልጣን**
Ethiopian Food and Drug Authority

**እዝል 6**

**በአዮዲን የበለጸገ የምግብ ጨውን በድጋሚ ማሸግ (ማምረት) ስራ ላይ የተሰማሩ መለስተኛ ድርጅቶች ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች የኢንስፔክሽን ቼክ ሊስት**

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. **የድርጅቱ ስም** ______________________ **የምርት ዓይነት** ____________________<br>2. **ድርጅቱ የሚገኝበት አድራሻ ክልል** ____________ **ዞን/ክፍለከተማ** _________<br>**ወረዳ** _________ **ከተማ** _____________ **ቀበሌ** ___________<br>**የቦታው ልዩ መጠሪያ** _____________ **ስልክ ቁጥር** _________<br>3. **የድርጅቱ ባለቤት/ተወካይ** ______________________________ | | | |
| **ተ.ቁ** | **ሙሉ በሙሉ መኖር የሚያስፈልጉ መስፈርቶች** | **አለ** | **የለም** |
| **የባለሙያ ሁኔታ** | | | |
| 1) | በምግብ ምክንያት ከሚተላለፉ በሽታዎች ነፃ ስለመሆናቸው ህጋዊ የጤና ተቋም የቀረበ ማስረጃ ስለመኖሩ | | |
| 2) | የምርትና የጥራት ክፍል ባለሙያ | | |
| **አስፈላጊ ሰነዶች** | | | |
| 3) | የፋብሪካው ዝርጋታ (Factory Lay-out) | | |
| 4) | የምርት ፍሰት ሂደት (Process Flow Diagram) | | |
| **ዝርዝር መስፈርቶች** | | **የተቀመጠለት ውጤት** | **የተሰጠው ወጤት** |
| **ስለ ማምረቻ ቦታ ሁኔታ** | | 48 | |
| 5) | ፋብሪካው የተቋቋመበት አካባቢ የሚመረተውን በአዮዲን የበለጸገው የምግብ ጨውን ሊበክሉ ከሚችሉ በካይ ነገሮች ተጋላጭነት ሁኔታ | 5 | |
| 6) | የማምረቻ ህንፃው በአመራረት ሂደት በምርቱ ላይ ተፅእኖ በማያሳድር ሁኔታ ስለመገንባቱ | 6 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 7) | የጨው ማምረቻና ማከማቻ ክፍሎቹ ስፋት ለጨው ምርት፣ የጥሬ እቃና ምርት ማከማቻ፣ የጥራት ቁጥጥር ላቦራቶሪ በቂ ቦታ የያዘ እና የጨው ምርቱን የማይበክል መሆኑ | 10 | |
| 8) | የክፍሎቹ ግድግዳ ሊጸዳና ወለሉ ሊታጠብ የሚችል፤ በቀላሉ የጨው ምርቱን ሊበክል የሚችል በካይ ነገር የማይዝ ስለመሆኑ | 6 | |
| 9) | ህንፃው ሙቀት አምቀው ከሚይዙና በአጠቃላይ በክፍሉ ሙቀት ላይ ተፅእኖ ከማያሳድር ቁሳቁስ የተገነባ ስለመሆኑ | 4 | |
| 10) | የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻዎችን ለማስወገድ የሚያስችል ስርዓት መኖሩ | 3 | |
| 11) | በክፍሎቹ ውስጥ በቂ ብርሃንና የአየር ዝውውር ስለመኖሩ | 4 | |
| 12) | በአዮዲን የበለጸገ ጨው ምርቱን የቅዝቃዜ ሰንሰለት መጠበቂያ ቬንትሌተር ወይም አየር ኮንዲሽነር መኖሩ | 10 | |
| **ስለ ፋሲሊቲ ሁኔታ** | | **13** | |
| 13) | የደርቅና የፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያና በአግባቡ ለመያዝ የሚስችል ማቴሪያል ስለመኖሩ | 4 | |
| 14) | የሰራተኞች የደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁስ (ነጭ ጋዎን፣ጓንት፣ቱታ፣ የፀጉር መሸፈኛ፣ የአፍ ማስክና የመሳሰሉት የደህንነት አልባሳት ስለመኖራቸው) | 6 | |
| 15) | ድንገተኛ አደጋዎች ሲከሰቱ ለማካምና ለመቆጣጠር የሚያስችል የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ስለመኖሩ | 3 | |
| **ስለ ማምረቻ ማሽነሪ ሁኔታ** | | **39** | |
| 16) | ድርጅቱ ለማምረት የሚያስችሉ የተሟሉና ከዝገት የፀዱ፣ ከስቴንለስ ስቲል ወይም በጨዉ ላይ ምንም ዓይነት ለውጥ ሊያስከትል ከማይችል ማቴሪያል /Food Grade/ የተሰሩ ማሽኖች ስለመኖራቸው | 10 | |
| 17) | ድርጅቱ የሚረከበውን አዮዳይዝድ ጨው መርምሮ ለመቀበልም ሆነ ምርቱን በሚያመርትበት ወቅት መሰረታዊ ምርመራዎችን ለማድረግ የሚያስችል የላብራቶሪ (sieve analyzer, RTK or WYD or Titration or other) መመርመሪያ መሳሪያዎች ስለመኖራቸው | 8 | |
| 18) | የሚመረቱ የምርት ዓይነት የጥራት ቁጥጥር ለማካሄድ የሚያስችል የታሰረ ውል ስለመኖሩ | 8 | |
| 19) | የተመረተውን አዮዲን የተጨመረበት ጨው ለመመዘንና ለማሸግ የሚያስችል መሳሪያ መኖሩ | 8 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 20) | በምርቱ ማሸጊያ ላይ የመጠቀሚያ ጊዜና የባች ቁጥር ለማተም ወይም ለመጻፍ የሚያስችል መሳሪያ ስለመኖሩ | 5 | |
| | **ጠቅላላ ድምር** | 100 | |

የኢንስፔክተሮች አስተያየት

የኢንስፔክተሮች ስም ፊርማ የኢንስፔክሽን

ሀ. ___________________________ _______ ቀን ሰዓት

ለ. ___________________________ _______ _____________ _________

ሐ. ___________________________ ________

የኃላፊው አስተያየት፡

ስም ___________________________

ፊርማ _____________

ቀን _____________

ሰዓት _____________

የኢትዮጵያ የምግብና የመድኃኒት ባለልጣን
Ethiopian Food and Drug Authority

<u>እዝል 7</u>

## በአዮዲን የበለጸገ ጨው የሚያመርቱ መካከለኛና ከፍተኛ አምራች ድርጅቶች ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች የኢንስፔክሽን ቼክ ሊስት

| | | | |
|---|---|---|---|
| **የድርጅቱ ስም ____________________ የምርት ዓይነት __________________** <br> **ድርጅቱ የሚገኝበት አድራሻ ክልል ___________ ዞን/ክፍለከተማ ________** <br> **ወረዳ ________ ከተማ ____________ ቀበሌ __________** <br> **የቦታው ልዩ መጠሪያ ____________ ስልክ ቁጥር ________** <br> **የድርጅቱ ባለቤት/ተወካይ _____________________________** | | | |
| **ተ.ቁ** | **ካልተሟሉ የብቃት ማረጋገጫ የማያሰጡ ጉዳዮች** | **አለ** | **የለም** |
| 1) | በምግብ ምክንያት ከሚተላለፉ በሽታዎች ነፃ ስለመሆናቸው ህጋዊ የጤና ተቋም የቀረበ ማስረጃ ስለመኖሩ | | |
| 2) | የምርት ክፍል ባለሙያ | | |
| 3) | የፊዚኮ ኬሚካል ላብራቶሪ ባለሙያ | | |
| **አስፈላጊ ሰነዶች** | | | |
| 4) | የማሽነሪዎች ዝርጋታና ተከላ ዲዛይን (machineries installation or lay-out) ሰነድ | | |
| 5) | የምርት ፍሰት ሂደት (process flow diagram) | | |
| 6) | የማምረቻ ተቋም ፕላን ቅጂ ሰነድ | | |
| **ዝርዝር መስፈርቶች** | | **የተቀመጠለት ውጤት** | **የተሰጠው ወጤት** |
| **ስለ ማምረቻ ቦታ ሁኔታ** | | 45 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 7) | ፋብሪካው የሚቋቋምበት አካባቢና ግቢ በአዮዲን የበለጸገ የጨው ምርቱን ሊበክሉ ከሚችሉ በካይ ነገሮች ተጋላጭነት | 4 | |
| 8) | የማምረቻ ህንፃው ዲዛይን፣ የተገነባበት ማቴሪያልና የህንጻው አቀማመጥ በጨው ምርት አመራረት ሂደት ላይ ተፅእኖ በማያሳድር ሁኔታ የተገነባ ስለመሆኑ፤ | 6 | |
| 9) | የማምረቻና ማከማቻ ክፍሎቹ ስፋት ድርጅቱ ለጨው ምርቱ በቂ ሆኖ ቢያንስ የጥሬ እቃና ምርት ማከማቻ፣ የማምረቻ፣ የፊዚኮ ኬሚካል ጥራት ቁጥጥር ላቦራቶሪ የያዘ በቂ ቦታ እና የጨው ምርቱን የማይበክል ስለመሆኑ | 10 | |
| 10) | የሚመረተውን በአዮዲን የበለጸገ ጨው የቅዝቃዜ ሰንሰለት በጠበቀ ሁኔታ ለማከማቸት የሚያስችል የቅዝቃዜ ሰንሰለት መጠበቂያ ቬንትሌተር ወይም አየር ኮንዲሽነር መኖሩ | 8 | |
| 11) | የክፍሎቹ ግድግዳ ሊጸዳና ወለሉ ሊታጠብ የሚችል፤ በቀላሉ የጨው ምርቱን ሊበክል የማይችል ስለመሆኑ | 7 | |
| 12) | የውሃና ሌሎች ፍሳሾች ለማስወገድ የሚያስችል ዝግ የሆኑ የቆሻሻ ማስወገጃ መስመሮች ስለመኖራቸው | 5 | |
| 13) | በክፍሎቹ ውስጥ በቂ ብርሃንና የአየር ዝውውር ስለመኖሩ | 5 | |
| **ፋሲሊቲ ሁኔታ** | | **15** | |
| 14) | የደረቅና የፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያና በአግባቡ ለመያዝ የሚስችል ማቴሪያል ሁኔታ | 4 | |
| 15) | የሰራተኞች የደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁስ፣ ነጭ ጋዎን፣ ጓንት፣ ቱታ፣ የፀጉር መሸፈኛ፣ የአፍ ማስክና የመሳሰሉት የደህንነት አልባሳት ስለመኖራቸው | 7 | |
| 16) | ድንገተኛ አደጋዎች ሲከሰቱ ለማከምና ለመቆጣጠር የሚያስችል የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ስለመኖሩ | 4 | |
| **ስለ ማምረቻ ማሽነሪ ሁኔታ** | | **40** | |
| 17) | ድርጅቱ ለማምረት የሚጠቀምባቸው ማሽኖች ከዝገት የፀዱ፣ ከስቴንለስ ስቲል ወይም በጨው ምርቱ ለውጥ ሊያስከትል ከማያስከትል ማቴሪያል /Food Grade/ ስለመሰራታቸው | 8 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 18) | ለጨው ምርቱ የጥራት ቁጥጥር ለማካሄድ የሚያስችል የፊዚኮ ኬሚካል ጥራት የምርመራ (sieve analyzer, RTK or WYD or Titration or other) መመርመሪያ መሳሪያዎች ስለመኖራቸው | 8 | |
| 19) | የሚመረቱ የምርት ዓይነት የጥራት ቁጥጥር ለማካሄድ የሚያስችል የታሰረ ውል ስለመኖሩ | 6 | |
| 20) | የተመረተውን አዮዲን የተጨመረበት ጨው በአግባቡ ለማሸግ የሚያስችል መሳሪያ መኖሩ | 7 | |
| 21) | የቅዝቃዜ ሰንሰለት በጠበቀ መልኩና፣ጨው የማይበክልና በውስጡ ያለውን የአዮዲን መጠን ሊያባክን (ሊቀንስ) ለማጓጓዝ የሚያስችል ስርዓት መኖሩ | 5 | |
| 22) | በምርቱ ማሸጊያ ላይ የመጠቀሚያ ጊዜና የባች ቁጥር ለማተም ወይም ለመጻፍ የሚያስችል መሳሪያ ስለመኖሩ | 6 | |
| | ጠቅላላ ድምር | 100 | |

የኢንስፔክተሮች አስተያየት

_______________

_______________

| የኢንስፔክተሮች ስም | ፊርማ | የኢንስፔክሽን ቀን | ሰዓት |
|---|---|---|---|
| 1. ______________________ | ________ | | |
| 2. ______________________ | ________ | ______________ | __________ |
| 3. ______________________ | __________ | | |

የኃላፊው አስተያየት

_______________

_______________

ስም ______________________

ፊርማ ____________

| |
|---|
| ቀን ____________<br>ሰዓት ____________ |

የኢትዮጵያ የምግብና የመድኃኒት ባለልጣን
Ethiopian Food and Drug Authority

እዝል 8

## በአዮዲን የበለጸገ ጨው ላኪ፣አስመጪ ወይም በጅምና አከፋፋይ ድርጅቶች ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

## የኢንስፔክሽን ቼክ ሊስት

| የድርጅቱ ስም ______________________የምርት ዓይነት ____________________<br>ድርጅቱ የሚገኝበት አድራሻ ክልል _____________ ዞን/ክፍለከተማ _________<br>ወረዳ _________ ከተማ ______________ ቀበሌ ____________<br>የቦታው ልዩ መጠሪያ ______________ ስልክ ቁጥር _________<br>የድርጅቱ ባለቤት/ተወካይ _________________________________ | | | |
|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | ካልተሟሉ የብቃት ማረጋገጫ የማያሰጡ ጉዳዮች | አለ | የለም |
| 23) | ቴክኒካል ባለሙያው በምግብ ምክንያት ከሚተላለፉ በሽታዎች ነፃ ህጋዊ የጤና ተቋም የቀረበ ማስረጃ ስለመኖሩ | | |
| 24) | የቴክኒካል ባለሙያ | | |
| አስፈላጊ ሰነዶች | | | |
| 25) | የስርጭት ስርአት መቆጣጠሪያ ሰነድ መኖሩ | | |
| 26) | ድርጅቱ በአዮዲን የበለጸገውን ምርት ሲገዛ የአምራች ድርጅቱ ፍቃድ ያለው መሆኑንና የጥራት ምርመራ ውጤት (Certificate of analysis) ሰነድ የተረከበ መሆኑ | | |
| 27) | የሚያሰራጨውን ጨው አስገዳጅ ደረጃውን ማሟላቱን ማረጋገጫ (checking system) ስርዓት ስለመኖሩ፤ | | |
| ዝርዝር መስፈርቶች | | የተቀመጠለት ውጤት | የተሰጠው ወጤት |
| ስለ ማከማቻ ህንጻ ሁኔታ | | 70 | |
| 28) | የማከማቻ ህንፃው ተገነባበት ግብአት በአዮዲን የበለጸገውን ጨው ለብክነትና ብክለት ተፅእኖ በማያጋልጥና በማያሳድር ሁኔታ የተገነባ ስለመሆኑ፤ | 8 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 29) | የህንፃው ስፋት የበለጸገውን ጨው ለማከማቸትና ጥቅም ላይ የማይውል ጨው ማቆያ በቂ የሆነ ቦታ መኖሩ፤ | 15 | |
| 30) | የህንፃው ወለልና በቀላሉ ሊፀዳ የሚችልና ውሀ በማያቁር መልኩ የተሰራ መሆን አለበት፤ | 9 | |
| 31) | የክፍሉ ጣሪያ ሙቀት ሊቀንስ ከሚችል ማቴሪያል የተሰራ ወይም ከፍ ብሎ የተሰራና ቀጥተኛ የፀሐይ ብርሃንና ዝናብ የማያስገባ መሆኑ፤ | 7 | |
| 32) | በአዮዲን የበለጸገ ጨው ለማከማቸት የሚያስችል የቅዝቃዜ ሰንሰለት መጠበቂያ ቬንትሌተር ወይም አየር ኮንዲሽነር መኖሩ | 10 | |
| 33) | የክፍሎቹ ግድግዳ በቀላሉ ሊጸዳና ወለሉ ሊታጠብ የሚችል፤ የጨው ምርቱን ሊበክል የማይችል መሆኑ፤ | 11 | |
| 34) | በክፍሎቹ ውስጥ በቂ ብርሃንና የአየር ዝውውር (የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ) ስለመኖሩ | 10 | |
| **ፋሲሊቲ ሁኔታ** | | **30** | |
| 35) | የደረቅ ቆሻሻ በአግባቡ ለማጠራቀሚያና ለማስወገድ የሚስችል ቁስ መኖሩ | 6 | |
| 36) | ድንገተኛ አደጋዎች ሲከሰቱ ለማከምና ለመቆጣጠር የሚያስችል የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ስለመኖሩ | 7 | |
| 37) | የሰራተኞች የግል ደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁሶች (የስራ ኮት፣የእጅ ጓንትና ሌሎች ማቴሪያሎች መኖራቸው ): | 9 | |
| 38) | በማጓጓዝ ወቅት የምግብ ጨውን ሊበክልና በውስጡ ያለውን የአዮዲን መጠን ሊያባክን (ሊቀንስ) የሚችል ስርዓት መኖሩ□ | 8 | |
| | ጠቅላላ ድምር | 100 | |

የኢንስፔክተሮች አሰተያየት

የኢንስፔክተሮች ስም ፊርማ የኢንስፔክሽን

4. ______________________ _______ ቀን ሰዓት

5. ______________________ _______ ______________ ________

6. ______________________ _________

የኃላፊው አስተያየት

ስም ______________________________

ፊርማ ______________

ቀን ______________

ሰዓት ______________